የCambridge ከተማ አስተዳደር የምርጫ ኮሚሽነሮች ቦርድ

51 Inman Street፣ Cambridge፣ MA 02139 • ስልክ፦ 617-349-4361
ፋክስ፦ 617-349-4366 • ኢሜይል፦ elections@cambridgema.gov

**ኮሚሽነሮች፦**
Ethridge A. King, Jr.
Larry W. Ward
Charles J. Marquardt
Thomas J. Stohlman, Jr.

**ዋና ዳይሬክተር፦**
Tanya L. Ford

**ረዳት ዳይሬክተር፦**
Lesley Waxman

በቅድሚያ የተሰናዳ ኤስ.ቲ.ዲ
የUS ፖስታ አገልግሎት
የተከፈለበት
CAMBRIDGE MA
የፈቃድ ቁጥር 58215

ነዋሪ ደንበኛ
Cambridge, MA

# እ.ኤ.አ ለሴፕቴምበር 3 ቀን 2024 ዓ.ም የመጀመሪያ ዙር ምርጫ
# አስቀደሞ ድምፅ የመስጫ መመሪያ
## በCAMBRIDGE ከተማ

**እ.ኤ.አ ለሴፕቴምበር 3 ቀን 2024 ዓ.ም የመጀመሪያ ዙር የELECTION COMMISSION (ምርጫ ኮሚሽን) የስቴት ምርጫዎች የ24-ሰዓት ይፋዊ ድምፅ መስጫ ሳጥን መገኛዎች**

## ዋና ዋና የድምፅ መስጫ ሳጥን መገኛዎች

**የሚከተለው ቦታ እ.ኤ.አ ከዓርብ ኦገስት 9 ቀን 2024 ዓ.ም ጀምሮ የምርጫ ቀን እስከሚውልበት እ.ኤ.አ ማክሰኞ ሴፕቴምበር 3 ቀን 2024 ዓ.ም ድረስ ክፍት ይሆናል። ይህ የድምፅ መስጫ ሳጥን ቦታ እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር 3 ቀን 2024 ዓ.ም በሚውለው የምርጫ ቀን ላይ ክፍት የሚሆነው ብቸኛው ቦታ ነው።**

**Coffon ሕንፃ**
*51 Inman Street*
በፊት ለፊት መግቢያ በሩ የቀኝ ጎን በኩል

## ድምፅ መስጫ ሳጥን የሚገኝባቸው ሌሎች ቦታዎች

**የሚከተሉት ቦታዎች ከዓርብ እ.ኤ.አ ኦገስት 9 ቀን 2024 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኞ እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር 2 ቀን 2024 ዓ.ም ድረስ ክፍት ይሆናሉ። ምርጫው በሚካሄድበት ቀን እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር 3 ቀን 2024 ዓ.ም ላይ ሌሎች የድምፅ መስጫ ሳጥን ቦታዎች ክፍት አይሆኑም።**

**City Hall**
*795 Massachusetts Avenue*
ከኋለኛው መግቢያ በር አቅራቢያ

**Morse ትምህርት ቤት**
*40 Granite Street*
ከፊት ለፊት መግቢያ በሩ አቅራቢያ

**Cambridge Police Headquarters (የCambridge ፖሊስ ዋና መሥሪያ ቤት)**
*125 6th Street*
ከሕንፃው ፊት ለፊት አቅራቢያ

**Maria L. Baldwin ትምህርት ቤት**
*85 Oxford Street*
ከ*Oxford Street* መግቢያ በሩ በስተቀኝ

**O'Neill ቤተ-መጻሕፍት**
*70 Rindge Avenue*
ከመግቢያው ደረጃዎች አጠገብ

እባክዎ ፖስታውን ወደ ድምፅ መስጫ ሳጥኑ ከማስገባትዎ በፊት የመረጡበት ድምፅ መስጫ ወረቀት በጁራት ፖስታው (ቢጫ ቀለም ባለው ፖስታ) ውስጥ መታሸጉን እና በጁራት ፖስታው ላይ ባለው ማረጋገጫ ላይ ፊርማ እንዳረፈበት ያረጋግጡ።

## በብዙ ቋንቋ የተጠናቀሩ

বাংলা | አማርኛ | عربي
ESPAÑOL | 中文 | PORTUGUÊS
KREYÒL AYISYEN | ENGLISH

# አስቀድመው ድምፅ ይስጡ! እጩዎን በፖስታ ይምረጡ!

የCambridge Election Commission እርስዎ በሚመችዎ መርሃ ግብር መሠረት ለመምረጥ ቀላል እና አመቺ እንዲሆንልዎ እያመቻቸ ይገኛል። በፖስታ ወይም በአካል በመቅረብ አስቀድመው ድምፅ ይስጡ!




### በአካል በመቅረብ አስቀድሞ ድምፅ መስጠት የሚቻልበት ጊዜ

እ.ኤ.አ ከኦገስት 24 እስከ ኦገስት 30 ቀን ድረስ ድምፅ መስጫ ጊዜዎችን እና ቦታዎችን ለማግኘት ከውስጥ ይመልከቱ!

## የመራጭ ምዝገባ

**በኢንተርኔት፦** www.RegisterToVoteMA.com
የሞተር ተሽከርካሪዎች መዝገብ መታወቂያ (Registry of Motor Vehicles ID) ከሌለዎት መመዝገቢያ ቅጽዎን አትመው 51 Inman St፣ Cambridge MA፣ 02139 ወደሚገኘው Election Commission Office በፖስታ መላክ ይኖርብዎታል።

**በአካል፦**
በ*Cambridge Election Commission፣ 51 Inman Street፣ Cambridge, MA 02139* በመደበኛ የሥራ ሰዓታት።

እ.ኤ.አ ኦገስት 24 ቅዳሜ ቀን ላይ በየትኛውም አስቀድሞ ድምፅ መስጫ ቦታ ላይ ከ9 ኤ.ኤም እስከ 3 ፒ.ኤም ወይም በElection Commission ቢሮ ከ9 ኤ.ኤም እስከ 5 ፒ.ኤም ድረስ መመዝገብ ይችላሉ።

**የመራጭነት ምዝገባ ሁኔታዎን ይፈትሹ**
www.RegisterToVoteMA.com
ወይም ለElection Commission Office በ617-349-4361 ይደውሉ።

**የመመዝገቢያ ወይም ስምዎን፣ አድራሻዎን ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎን የመለወጫ ቀነ-ገደቡ ቅዳሜ ኦገስት *24* ቀን ነው።**

# አስቀድሞ ድምፅ የመስጠት ሂደትን

## አስቀድሞ ድምፅ መስጠት ምንድነው?

አስቀስሞ ድምፅ መስጠት ከምርጫ ቀኑ በፊት ድምፅ መስጠት የሚቻልበት ዕድል ነው። በአካልም ሆነ በፖስታ ድምፅ መስጠት የሚችሉ ሲሆን፣ የድምፅ መስጫ ወረቀትዎም በምርጫ ቀኑ ገቢ ይደረግልዎታል። አስቀድሞ ድምፅ መስጫ ጊዜው በMassachusetts State Law (Massachusetts ስቴት ሕግ) መሠረት ተደንግጎ የተቀመጠ ነው።

## አስቀድሞ ድምፅ መስጠት የሚችለው ማን ነው?

Cambridge ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም የተመዘገበ መራጭ አስቀድሞ ድምፅ መስጠት በሚቻልባቸው ጊዜያቶች ላይ ድምፅ መስጠት ይችላል! በጣቢያው ሳይገኙ ድምፅ ከሚሰጥበት አሠራር (absentee voting) በተለየ መልኩ አስቀድመው ድምፅ ለመስጠት ሰበብ ወይም ምክንያት አያስፈልግዎትም!

## አስቀድሜ ድምፅ መስጠት የሚችለው የት ነው?

በምርጫ ቀኑ ላይ ከሚተገበረው አሠራር በተለየ መልኩ የምርጫ ጣቢያ አይመደብልዎትም። ከታች ከተዘረዘሩት የCambridge አስቀድሞ ድምፅ መስጫ ቦታዎች ውስጥ ወደ የትኛውም መሄድ ይችላሉ። በ51 Inman Street የሚገኘው የElection Commission ቢሮ ለመጀመሪያ ዙር የስቴት ምርጫዎች አስቀድሞ ድምፅ መስጫ ጣቢያ ሆኖ አያገለግልም።

## አስቀድሜ ድምፅ መስጠት የምችለው መቼ ነው?

አስቀድሞ ድምፅ መስጫ ጊዜው እ.ኤ.አ ከቅዳሜ ኦገስት 24 ቀን 2024 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አርብ ኦገስት 30 ቀን 2024 ዓ.ም ድረስ ይቆያል። አስቀድሞ ድምፅ መስጠት የሚቻልባቸው ሰዓታት ከቀን ቀን ሊለያዩ ስለሚችሉ ከዚህ በታች ያለውን መርሃ-ግብር ይመልከቱ።

## ከዚህ ይልቅ በምርጫ ቀኑ ላይ ደምጽ መስጠት ብፈልግስ?

አስቀድመው ድምፅ ካልሰጡ በምርጫ ቀኑ ወደተመደቡበት ድምፅ መስጫ ጣቢያ በመሄድ ድምፅ መስጠት ይችላሉ።
**እርስዎ የተመደበቡበት ድምፅ መስጫ ጣቢያ ተለውጦ ሊሆን እንደሚችል እባክዎ ይህን ልብ ይበሉ።**

የተመደቡበትን ምርጫ ጣቢያ የያዘ የመራጭ ማሳወቂያ ከምርጫ ቀኑ በፊት የሚደርስዎ ሲሆን፣ እንደ አማራጭም www.cambridgema.gov/pollinglocations ን በመጎብኘት የተመደቡበትን ጣቢያ መመልከት ይችላሉ።
የምርጫ ጣቢያዎች እ.ኤ.አ ማክሰኞ ሴፕቴምበር 3 ቀን 2024 ዓ.ም ላይ ከ7 ኤ.ኤም እስከ 8 ፒ.ኤም ክፍት ይሆናሉ። ድምፅ መስጠት የሚችሉት አንድ ጊዜ ብቻ ነው፤ አስቀድመው ድምፅ ከሰጡ በምርጫ ቀኑ ላይ ድምፅ መስጠት አይችሉም።

# በአካል በመቅረብ አስቀድሞ ድምፅ

| ቅዳሜ ኦገስት 24 | እሁድ ኦገስት 25 | ሰኞ ኦገስት 26 | ማክሰኞ ኦገስት 27 | ረቡዕ ኦገስት 28 | ሐሙስ ኦገስት 29 | አርብ ኦገስት 30 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 ኤ.ኤም - 3 ፒ.ኤም | 9 ኤ.ኤም - 3 ፒ.ኤም | 8:30 ኤ.ኤም - 8 ፒ.ኤም | 8:30 ኤ.ኤም - 5 ፒ.ኤም | 8:30 ኤ.ኤም - 5 ፒ.ኤም | 8:30 ኤ.ኤም - 5 ፒ.ኤም | 8:30 ኤ.ኤም - 12 ፒ.ኤም |

## በአካል በመቅረብ አስቀድሞ ድምፅ መስጠት

**Main Library** – *449 Broadway*
**Cambridge Water Department (የCambridge ውኃ መምሪያ ክፍል)** - *250 Fresh Pond Parkway*
**Valente ቤተ-መጻሕፍት**– *826 Cambridge Street፣ በBerkshire Street የጎን መግቢያ*

51 Inman Street ላይ የሚገኘው **የElection Commission Office** በመጀመሪያው ዙር የስቴት ምርጫ ላይ አስቀድሞ ድምፅ ለመስጠት ከሚያስችሉ የምርጫ ጣቢያዎች ተርታ **አይመደብም**። መራጮች ከላይ ከተዘረዘሩት አስቀድሞ ድምፅ መስጠት ከሚቻልባቸው የምርጫ ጣቢዎች ውስጥ ወደ አንዱ መሄድ ይኖርባቸዋል።

# በፖስታ መልዕክት አስቀድሞ ድምፅ

**1.**

ከwww.MailMyBallotMA.com ማመልከቻ ያውርዱ ወይም ስምዎን፣ የCambridge አድራሻዎን፣ ድምፅ መስጫ ወረቀቱ የሚላክበትን አድርሻ እና ፊርማዎን የያዘ የጽሑፍ ማመልከቻ ይላኩልን።
**ያልተመዘገቡ መራጮች የየትኛውን ፓርቲ ድምፅ መስጫ ወረቀት እንደሚፈልጉም መጥቀስ ይኖርባቸዋል።**

በዲሞክራቲክ ወይም ሪፐብሊካን ፓርቲ ውስጥ ከተመዘገቡ ድምፅ መስጠት የሚችሉት በተመዘገቡበት ፓርቲ ድምፅ መስጫ ወረቀት ላይ ብቻ ነው። በተለምዶ ገለልተኛ ተብለው ከሚጠሩት ያልተመዘገቡ ግለሰቦች ውስጥ የሚካተቱ ከሆነ በመጀመሪያው ዙር ምርጫ ላይ ድምፅ መስጠት የሚፈልጉበትን የፓርቲ ድምፅ መስጫ ወረቀት መርጠው ገለልተኛ እንደሆኑ መቀጠል ይችላሉ።

**2.**

የፈረሙበትን ማመልከቻ በኢሜይል፣ በፋክስ ወይም በፖስታ ይላኩ። ማመልከቻዎን በኢሜይል የሚልኩ ከሆነ በእጅዎ ከፈረሙት ፊርማዎ ጋር ሊነጻጸር በሚችል መልኩ አመሳስለው ፊርማዎን ማስቀመጥ ይገባዎታል። ኤሌክትሮኒክ ፊርማዎች፣ ስካን የተደረጉ ማመልከቻዎች እና የማመልከቻ ፎቶግራፎች ተቀባይነት ይኖራቸዋል። በኮምፒውተር የተተየቡ ፊርማዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

**ኢሜይል፡-** elections@cambridgema.gov
**ፋክስ፡-** 617-349-4366
**ፖስታ፡-** Cambridge Election Commission፣ 51 Inman Street Cambridge፣ MA 02139

**3.**

**ድምፅ መስጫ ወረቀትዎን መልሶ መላክ የሚችሉባቸው አማራጮች፡-**

- ከድምፅ መስጫ ወረቀትዎ ጋር የተሰጠዎትን ለፖስታ-የተከፈለበት ማሸጊያ በመጠቀም የድምፅ መስጫ ወረቀቱን መልሰው በፖስታ ይላኩ።
- በተቀመጡት አስቀድሞ ድምፅ መስጫ ሰዓታት ወደተመደበው አስቀድሞ ድምፅ የመስጫ ጣቢያ በመሄድ የታሸገውን ድምፅ መስጫ ፖስታ ለምርጫ ባለስልጣኑ ይመልሱ።
- ድምፅ መስጫ ወረቀትዎን Cambridge ውስጥ ከሚገኙት ስድስት (6) ድምፅ መስጫ ሳጥኖች ውስጥ በአንዱ ያስገቡ። በዚህ መመሪያ የመጨረሻ ገጽ ላይ ድምፅ መስጫ ሳጥኖች የሚገኙባቸው ቦታዎች በዝርዝር ተቀምጠዋል።



## አስፈላጊ ቀነ ገደቦች

**ድምፅ መስጫ ወረቀት መጠየቅ የሚቻልበት ቀነ ገደብ፡-** እ.ኤ.አ ኦገስት *26 ሰኞ ቀን 5 ፒ.ኤም።*
ማመልከቻዎ በወቅቱ መላኩን ለማረጋገጥ የElection Commission በተቻለ ፍጥነት እንዲያመለክቱ ይመክራል።

**ድምፅ መስጫ ወረቀት መመለስ የሚቻልበት ቀነ ገደብ፡-** እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር *3 ማክሰኞ ቀን 8 ፒ.ኤም።*

**ድምፅ መስጫ ወረቀትዎን በኦንላይን ይከታተሉ!**
www.TrackMyBallotMA.com

**ጥያቄዎች አሉዎት?**

ድረ-ገጻችንን CambridgeMA.gov/EarlyVoting ላይ ይጎብኙ
ለElection Commission Office በ617-349-4361 ይደውሉ
election@cambridgema.gov ላይ ኢሜይል ይላኩልን

ማመልከቻዎ ላይ እገዛ ፈልገው ከElection Commission ጋር ለመግባባት ግን አስተርጓሚ እንዲቀርብልዎ ከፈለጉ እባክዎ 617-865-2273 ላይ ይደውሉ። አስተርጓሚው ከከተማው አስተዳደር ተወካይ ጋር ያገናኝዎታል።